

# ዮሴፍና ወንድሞቹ

* ዮሴፍ በምድረ ግብፅ አገረ ገዢ ሆነ። በሥልጣን የመጀመሪያው ሰው ፈርኦን ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ዮሴፍ ነበር። ዮሴፍ ግብፃዊት ሚስት ተሰጠው ሁለት ልጆችንም ወለደችለት።

*ጥሩ ምርት በነበረባቸው 7 ዓመታት ዮሴፍ ሕዝቡ እህል እንዲያከማቹ አደረጋቸው። ከሰባቱ አመታት በኋላ ዝናብ አቆመ የእህል ምርትም ቆመ። በምድር ላይ ድርቁ እጅግ የበረታ ሆነ። በዚያን ጊዜ እህል የሚገኝባት አገር ግብፅ ብቻ ነበረች።

* ያዕቆብ እህል ይገዙ ዘንድ አስሩን ልጆቹን ወደ ግብፅ ላካቸው። ወንድማማቾቹ ለዮሴፍ ዝቅ ብለው በግንባራቸው ተደፍተው ሰገዱለት። ዮሴፍ ወንድሞቹ እንደሆኑ አወቀ። እነርሱ ግን አላወቁትም። ምግብ ሰጣቸው። ከእነርሱ አንደኛውን በወህኒ ቤት አኖረው። እንደገና ወደ ግብፅ ምድር ለእህል ሸመታ ሲመለሱ ታናሽ ወንድማቸውን ይዘው እንዲመጡ አዘዛቸው። ( ቢንያም የዮሴፍ ታናሽ ወንድሙ ነው።)

* ያዕቆብ ቢንያምን ለመላክ ፈራ። ሆኖም ወንድሞቹ እህል ለመሸመት ወደ ግብፅ ለሁለተኛ ጊዜ ሲሄዱ ቢንያምን ይዘውት ሄዱ። በዚህ ጊዜ ግን ዮሴፍ ለወንድሞቹ ራሱን ገለጠላቸው። ከዚህ በፊት በእርሱ ላይ ከፈፀሙት ክፋት የተነሳ ይበቀለናል ብለው ሰጉ። ዮሴፍ ግን ይቅር ባይ ነበር። በምድር ላይ የተከሰተው ድርቅ ገና ረዘም ላለ ጊዜ ስለሚቆይ ወደ ከነአን ምድር ተመልሰው አባታቸውንና ቤተሰቦቻቸውን ይዘው እንዲመጡ ነገራቸው።

* ስለ ዮሴፍ በሕይወት መኖር በሰማ ጊዜ ያዕቆብ እጅግ ደስ አለው። ያዕቆብና መላ ቤተሰቡ ወደ ግብፅ ወረዱ። ያዕቆብም እንደገና ማየት ቻለ።

* ድርቁ ለሰባት አመታት ቆየ። ግብፃውያን ያላቸው እህልና ገንዘብ አለቀባቸው። ስለዚህ ከብቶቻቸውንና እንስሶቻቸውን በእህል ለወጡ። ከዚህ የተነሳም ግብፃውያን በሙሉ የፈርኦን አገልጋዮች ሆኑ። ዮሴፍና ቤተሰቦቹ ግን ብዙ እህል ባለበት በጌሴም ምድር ተቀመጡ።

የዮሴፍና የወንድሞቹ ታሪክ የሚገኘው በዘፍጥረት 42፣43፣44፣45፣46፣ እና 47 ነው።